Case Comments

Case Comment 1

Judicial Assumption of Fact to Enable Prosecution's Creeping Case to Stand

Dejene Girma*

1. Introduction

Semper necessitas probandi incumbit ei qui agit is a Latin expression which essentially means he who asserts must prove. In justice systems around the world, it has been accepted that the burden of proof lies on someone who asserts something. Thus, in criminal cases, prosecutions must prove every fact they allege as bases of their cases and that are denied by the accused unless the burden of proof is expressly shifted to the accused by the law. For instance, if A claims that B intentionally killed C, A must prove that the act of B, which in reality was homicide, was committed intentionally. If this element is not proved, then the prosecution (A) will not have a case unless there is an alternative charge for negligence, which should also be proved in like manner. Now, in light of this mini introduction, the writer wants to present a comment on one case decided by the Federal High Court, Ledeta Bench, involving issuance of a cheque. In the case, the judge had to make a factual assumption to revive prosecution's dying case. Had it not been for that assumption, the accused would have been acquitted, which of course, should have happened given the prosecution's inability to prove the foundational fact it alleged for the existence of the alleged crime.

2. Summary of the material facts of the Case

On 02/02/2011 EC, a certain prosecutor representing the Federal Attorney General (FAG) instituted a criminal case against Mr. FD, the accused. In the case, the prosecutor claimed that the accused issued a cheque to his victim with the knowledge that his bank account from which the cheque could be cashed was closed and hence he committed a crime against article 692(1) of the Criminal Code. On his part, the accused entered a not-guilty plea. First, the accused denied that he knew his account from which the cheque could be cashed was closed

* LL.B, LL.M. PhD, Assistant Professor, School of Law and Federalism

at the time the cheque was issued. Second, the accused argued that he did not give the cheque to the alleged victim to take to a bank for cashing but to keep it with himself as a guarantee. As a result, the Bench asked the prosecutor what he intends to do next and the prosecution requested the judge to hear his witnesses. On the date fixed for witness hearing, the prosecution's witnesses were heard (two in number). However, none of the witnesses testified that the accused knew that his bank account to which the cheque issued was related was closed. The witnesses, one of whom was the alleged victim, simply testified that the concerned bank told them that the accused's account was closed when they took the cheque to the bank. Moreover, none of the prosecution's documentary evidence showed that the accused know about the closure of his account when the cheque was issued. Yet, the judge convicted the accused for violating article 692(1) of the Criminal Code and sentenced him to two years and three months rigorous imprisonment and 500 Birr fine. In the case, the judge stated that, although the prosecutor did not prove that the accused knew his bank account was closed at the time he issued the cheque, it is assumed that the accused knew his account was closed because, first, he is a business person and business persons know about their bank accounts, and, second, the closure of his account was ordered by the National Bank of Ethiopia as the result of repeating issuance of cheques with no sufficient cover. It is this reasoning of the court/judge that is worth commenting on in this work.

3. Discussion: Exposing the Extent of Judicial Bias to Help A Prosecution's Case

As stated above, the judge in charge of the case clearly stated that the prosecutor did not prove that the accused knew his bank account, to which the issued cheque was related, was actually closed. Yet the foundation of the charge is the knowledge of the accused about the status of his bank account. In the charge the prosecutor stated, "ተከሳሽ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት.....በማሰብ......ሂሳቡ.....የተዘጋ መሆኑን እያወቀ ለግል ተበዳይ.....ቼክ....ፅፎና ፈርሞ ከሰጠ በኋላ ተበዳይ ቼኩን....ለክፍያ ሲያቀርብ ሂሳቡ ተዘግቷል ተብሎ የተመለሰ በመሆኑ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ተከስሰዋል።" On the other hand, Mr. FD, the accused, had denied the charge. In this case, the basic and only thing the prosecution had to do was to introduce its evidence to show that the accused indeed knew that his account was closed at the time the cheque was issued. That would have sufficed to shift the burden of proof from the prosecution to the accused. Nevertheless, the prosecution was unable to do this; none of the evidence produced could tell that there was such knowledge on the side of the accused. This leaves the concerned judge with only one option; which is, to rule that the prosecution has

not, beyond reasonable doubt, established his case, or the fact in issue, and order the acquittal of the accused in accordance with article 141 of the Criminal Procedure Code.

Lamentably, however, the judge made the accused to produce his defence evidence, in accordance with article 142 of the Criminal Procedure Code, and the accused did. In his defence, the accused made a personal statement arguing that he did not know that his account was closed; he also used the prosecution's documentary evidence to show that the concerned bank did not let him know that his account was closed. Yet, the judge was already pre-disposed and he was not ready to accept the accused arguments. Instead, the judge engaged in what could be called un-judge like work, which is assuming a fact to help the prosecution win the case. This is a quintessential case of how prosecution-biased some trials could be.

In reality, the accused may have committed the alleged crime. Yet, if the accused denies the made against him by the prosecutor, it is for the prosecutor to prove each and every key fact in his charge. The judge has no business to assume a fact and rehabilitate the prosecution's crippling case. The only assumption that a judge has to accept is the assumption made by the law. For example, under article 3, the Corruption Crimes Proclamation N o.881/2015 allows a presumption as to the intent to obtain for oneself or to procure for another an undue advantage or to injure the right or interest of a third person when the material element of the crime is proved. From this, we can understand that law-makers make express permission when they want factual assumption to be made. Yet, article 692(1) of the Criminal Code does not make any such assumption. Thus, in the case at hand, the judge was like a substitute player on the bench because at the point/time the prosecutor was unable to prove the key fact that was alleged in the charge, he jumped in and made an unwarranted factual assumption to score a last minutes goal to help the prosecution win the case. So, the judge in this case was not acting like a judge; indeed, he was a prosecutor in a judge's gown thereby defeating the purpose of the principle of semper necessitas probandi incumbit ei qui agit (he who asserts must prove).

4. Conclusion

The above brief case comment shows the extent to which some judges may not be objective in handling criminal cases. In the case at hand, the accused might have committed the said crime but it is not for the judge to convict him by making an unwarranted factual assumption. There is absolutely no justification for a judge to participate in a case as a litigant. Unfortunately this is the reality we see in some cases in our criminal and that may be one

reason why some experts say our criminal justice system is prosecution-biased. Indeed, such approach/practice has multiple disadvantages. First, it violates the accused person's right to presumption of innocence as accused persons are deprived of this right before the prosecution rebuts the presumption. Second, it makes prosecutors dependant on judges' support and this may cultivate the feeling of recklessness. Third, it will be against judicial impartiality. Therefore, judges must all the time be guided by the evidence and only evidence set out before them by the prosecutor. They should never take a side with prosecutors simply because they have a strong feeling that the accused has committed a crime as their feelings have no place at all.

Case Comment 2

Misganaw Kifelew*

Absract

This comment criticizes the Federal Cassation Decision File No 188419 redered on September 25, 2012 Ethiopian Calendar and published on Federal Court Cassation Bench Decisions Vol 24 from page 251 to 256. The Case in brief was that the Employer of Ato Markos Gatro's sister in Lebanon had transferred money to Ethiopia via Abay Bank S.C.to the benefit of Ato Markos Gatero. But the money was paid to a wrong person who claimed to be the real Markos Gatero by producing a Kebele Identification Card which showed that he was Ato Markos Gatero. Although lower courts ruled that the Bank should still pay to the real receiver, the Supreme Cassation Division reversed the decision arguing that the Bank has done all that is expected of it. This critic argues that a debtor who pays to a wrong person can never escape liability by invoking its due diligence but only by showing that it paid to a legally entitled creditor. The Cassation erred because it applied an improper law (Banking Proclamation No. 592/2000 as amended by Proclamtion No.1159/2011 *i.e. banking regulation which intends to govern the relationship between a bank and a government rather than a bank and its clients. The relationship between a bank and its client is governed by banking transaction law in particular and contract law in general. The relationship between Ato Markos Gatero and Abay Bank S.C. is a contractual relationship and therefore; governed by the Contract Law.Ato Markos Gatero's Sister through her agent entered into a contract of transfer of money with Abay Bank S.C. and in this transfer contract Ato Markos Gatero was stipulated as a beneficiary. Accordingly, the relationship between Ato Markos Gatero and Abay Bank falls under rules of Civil Codde of 1960 whereby Ato Markos was creditor and the bank was a debtor. The law that governs payment to unqualified person is Article 1743 of the Civil Code. According to this Article payment to unqualified person releases the debtor only when the payment was on the basis of documents which are apparently legitimate (the document is not forged but the holder is not the real creditor). In the case of Ato Markos Gatero payment is made against forged documents and therefore; the bank bears the responsibility to make the second payment. It is the nature of the document presented(forged vs genuine) that can release the debtor from the obligations of the law.*

የገንዘቡ መክፈል ለማን እንደሚገባ

1. መግቢያ

ይህ ጽሁፍ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር መ/ቁ/188419 መስከረም 25 ቀን 2012 ዒ.ም(የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ቸሎት ዉሳኔዎች

* LL.B, LL.M., PhD, Assistant Professor, School of Law and Federalism, ECSU.

ቅጽ 24 ከገጽ 252-256) በከሳሽ አቶ ማርቆስ ጋትሮ እና በተከሳሽ አባይ ባንክ አ.ማ መካከል በነበረዉ የፍትሀብሄር ክርክር ላይ የሰጠዉን የሰበር ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ የፍርድ ትችት ነዉ፡፡የሰበር አቤቱታዉን ያቀረበዉ ተከሳሽ ሲሆን የሰበር አቤቱታዉም ዋና ጭብጥ ባለእዳ እዳቸዉን(ገንዘብ) የከፈሉት የተጭበረበረ መታወቂያ በመያዝ ዋና ባለገንዘብ መስሎ ለተቀበለ ሰዉ ስለሆነ ክፍያዉን በመክፈል ሂደት ባንኩ ያጠፋዉ ጥፋት ስለሌለ ክፍያዉ ለትክክለኛዉ ባለገንዘብ እንደተከፈለ ይቆጠራል፤ምክንያቱም መታወቂያዉ የተጭበረበረም እንኳ ቢሆን ያ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት መንገድ ስለሌለና ለመጭበርበሩ የባንኩ አስተዋጽኦ የለም የሚል ብቻ ሳይሆን ሊኖር የሚችልበት እድልም የለም፤ ይልቁንም መጭበርበሩ የተፈጠረዉ ትክክለኛ ባለገንዘብ ነኝ ባይ የሚስጥር ቁጥር አሳልፈዉ ለሌላ ሰጥተዉ ቢሆን ነዉ የሚል ነበር፡፡ሰበር ሰሚዉም ይህንን ምክንያት ተቀብሎ በታችኞቹ ፍርድ ቤቶች የተሠጠዉን ዉሳኔ ሽሯል፡፡ይህ የፍርድ ትችት የሰበር ሰሚዉ ዉሳኔ ህግን የጣሰ ነዉ የሚል ትችት ያቀርባል፡፡

የትችቱም አጠቃላይ ይዘትም፡ የሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመፍታት የሚያስችል የህግ ምንጭ(appropriate source of law) አለልተከተለም የሚል ነዉ፡፡ ይህም ማለት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመወሰን እንደመነሻ መያዝ የነበረበት የፍትሐ ብሔር ሕግ መሰረት መሆን ሲገባዉ የባንክ ስራ አዋጅን እንደ ዋና የሕግ ምንጭ መጠቀሙ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ባለቤት መሰሎ ለታየ ሰዉ መክፈል ባለእዳዉን ከእዳዉ ነጻ የሚያደርገዉ ባለገንዘብ መስሎ የቀረበዉ ሰዉ ባለገንዘብ ያስመሰለዉ የያዘዉ ሕጋዊ ሰነድ(ያልተጭበረበረ ሰነድ) ሲሆን ብቻ ሆኖ እያለ የተጭበረበረ ሰነድ ላቀረበ ሰዉ መክፈልም ከእዳ ነጻ ያወጣል መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡

2. በክርክሩ በማስረጃ የተረጋጠ ፍሬ ነገር ጥቅል ይዘት

የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የአቶ ማርቆስ ጋትሮ እህት ለተጠሪ(ለወንድሟ) ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ10/12/2018) ከሊባኖስ ሀገር በአሰሪዋ በአቶ ኤሊያስ ኢሌሀበር አማካይነት በዌስተርን ዩኒየን ገንዘብ መሊኪያ አማካኝነት ስድስት መቶ ሰባ አምስት ዶላር ልካለት ነበር፡፡ የሚስጥር ቁጥሩንም ላኪ ለተቀባይ በስልካቸዉ ልካለት ነበር፡፡ ይህንኑ የሚያሳይ ማስረጃ ከኢትዮ ቴሌኮም ቀርቧል፤፤ነገር ግን ይህን ገንዘብ የተቀበለዉ ማርቆስ ጋትሮ ነኝ በማለት ሀሰተኛ መታቂያ ይዞ የቀረበ ሰዉ ነዉ፡፡

3. ፍርድ ቤቱ ግምት የተወሰደባቸዉ ፍሬ ነገር

ማርቆስ ጋትሮ ነኝ በማለት የተጭረበረ የቀበሌ መታወቂያ አቅርቦ ገንዘቡን የተቀበለዉ ግለሰብ የሃዋላ ገንዘብ ላኪዎች ለገንዘብ ተቀባይ ብቻ እንዲገልጹ የሚገባቸዉን ትክክለኛ የሚስጥር ቁጥር ለባንኩ አሳይቷል፡፡

4. የተከራካሪዎች ሙግት አጠቃላይ ይዘት

የአቶ ማርቆስ ጋትሮ(እዉነተኛ ባለገንዘብ) ክርክር ክፍያዉ የተከፈለዉ ሀሰተኛ ሰነድ(መታቂያ) ለያዘ ሰዉ ስለሆነ ባንኩ ግዴታዉን እንዳልተወጣ ይቆጠራል የሚል ነዉ፡፡ ባንኩ በበኩሉ ክፍያዉ የተከፈለዉ ትክክለኛ ላልሆነ ሰዉ መሆኑን አምኖ ጥፋተኛ ስላልሆነ ግን (ምክንያቱም ባንኩ በሀዋላ የተላከ ገንዘብ ለመክፈል ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ አድጓል-መታወቂያና የሚስጥር ቁጥር አረጋጧል፡፡) በመክፈሉ ምክንያት ግዴታዉን እንደተወጣ ይቆጠራል፤ይልቁንም ለዚህ ችግር ተጠያቂዉ እራሱ አቶ ማርቆስ ጋትሮ በመሆኑ ክፍያዉን እንደተቀበለ ሊቆጠር ይገባል የሚል ነዉ፡፡ ባንኩ አቶ ማርቆስ ጋትሮ እንደጥፋተኛ የሚቆጥረዉ የሚስጥር ቁጥሩን ለሌላ ሰዉ የሰጠዉ እራሱ አቶ ማርቆስ ነዉ(በቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ) በሚል እምነት ነዉ፡፡

5. ሰበር ሰሚዉ የመረመረዉ የህግ ጭብጥ ና የዉሳኔዉ ምክንያት

ፍርድቤቱ የመረመረዉጭብጥ ባንኩ ጥፋት አለበት ወይ የሚል ሲሆን ጥፋት መኖር አለመኖሩንም ለመወሰን ያጣራዉ "ባንኩ ክፍያዉን የፈጸመዉ የባንክ ስራ የሚጠይቀዉን አሰራርና ስርዓት በመከተል ነዉን?" የሚለዉን ነዉ፤፤ ባንኩ ክፍያዉን የፈጸመዉ የባንከ ስራ የሚጠይቀዉን አሰራርና ስርአት በመከተል በመሆኑ በክፍያዉ ሂደት የፈጸመዉ ጥፋት የለም ስለዚህም የከፈለዉ ክፍያ ለትክክለኛዉ ባለመብት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ወስኗል፡፡

6. ሰበር ሰሚዉ የፈጸማቸዉ የሕግ ስህተቶች

ከላይ በመግቢያዉ እንደተመለከተዉ ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት በሶስት ደረጃ የህግ ስህተት ፈጽሟል፡፡ የመጀመሪያዉ ክርክሩ ሊወሰንበት የሚገባዉን ሕግ ሲመርጥ ነዉ፡፡ ክርክሩ መፈታት የነበረበት በዉል ህግ መሰረት ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ግን የባንክ አስተዳደር አዋጅን መሰረት በማድረግ ክርክሩን መወሰኑ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ስህተት ደግሞ ገንዘብ ከፋይ ጥፋት እስካልተገኘበት ድረስ ክፍያዉ ለትክክለኛዉ ባለገንዘብ ባይደርስም እንኳ እንደከፈለ

ይቆጠራል ማለቱ ነዉ። እንዚህን ነጥቦች እንደቅደም ተከተላቸዉ እንደሚከተለዉ ለማሳየት እሞክራለሁ።

6.1 ክርክሩ ሊመራ ይገባ የነበረዉ በዉል ሕግ እንጂ በባንክ አስተዳደር አዋጅ መሰረት አለመሆኑን በሚመለከት

እንደሚታወቀዉ የባንክ ስራ በሁለት አይነት ህጎች ይገዛል። አንደኛዉ አይነት ሕግ የባንክ ስራዎች ዉል ሕግ ነዉ። የባንክ ስራዎች ዉል ሕግ በባንክና በደንበኞቻቸዉ መካከል ያለዉን ግንኙነት የሚገዛ ሕግ ነዉ። ይህ ግንኙነት የሚመራዉ በንግድ ሕግ ቁጥር 896 እስከ 976 ድረስ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች በቂ ካልሆኑ ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1676(1) በግልጽ እንደተመለከተዉ ከቁጥር 1675 እስከ 2026 ያሉት የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እንደማሟያ ሆነዉ ያገለግላሉ። በመሆኑም አንድ የባንክ ደንበኛ በባንኩ ላይ በቀጥታ ለፍርድ ቤት የሚያቀርበዉ ክስ የሚመራዉ በባንክ ስራዎች ዉል ሕግ ነዉ ማለትም በንግድ ሕግ ቁጥር 896 እስከ 976 ድረስ በተደነገጉት ድንጋጌዎች ማለት ነዉ። እነዚህ ድንጋጌዎች በቂ ባልሆኑ ጊዜ ደግም ስለዉል በጠቅላላዉ የተደነገገዉ የፍትሐ ብሔር ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነዉ።ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት እንዳመለከተዉም በአቶ ማቲዎስ ጋትሮ(የሰበር ተጠሪ) እና በአባይ ባንክ አ.ማ. መካከል ያለዉ ክርክር የባንክ ስራዎች ዉል ክርክር ነዉ። አቶ ማቲዎስ ጋትሮ በቀጥታ በባንኩ ላይ ክስ ያቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ የክርክሩ መሰረት የሆነዉ ጉዳይ የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል ነዉ።በመሆኑም መመራት ያለበት በንግድ ሕግ ቁጥር 896 እስከ 976 ነዉ። ይህ የማይበቃ ከሆነ ደግሞ ጉድለቱ የሚሞላዉ በፍትሐ ብሔር ሕግ ስለዉል በጠቅላላዉ በሚለዉ ሕግ ነዉ።

ሁለተኛዉ አይነት ሕግ የባንክ ስራ አስተዳደር ሕግ ሲሆን የባንክ ስራዎችን በሚመለከት መንግስት ስለሚያደርገዉ ቁጥጥርና ክትትል የሚደነግግ ሕግ ነዉ። ይህ ሕግ በባንክና በመንግስት መካከል ሊኖር የሚገባዉን ግንኙነት የሚመራ ሕግ ነዉ። ይህን የሚመለከተዉ ሕግ የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000(በአዋጅቁጥር 1159/2011 እንደተሻሻለዉ) ነዉ። በዚህ ሕግ መሰረት የባንኮች ተጠያቂነት ለደንበኞቻቸዉ ሳይሆን ለብሔራዊ ባንክ ነዉ።ባንኮች የባንክ ስራ አዋጅም ሆነ በአዋጁ መሰረት በሚኒስትሮች ምክርቤት የወጡ ደንቦችን ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወጡት መመሪያዎች ጥሰዉ ቢገኙ ተጠያቂነታቸዉ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ነዉ እንጂ ለደንበኛቸዉ አይደለም። የሚወሰድባቸዉም እርምጃም አስተዳደራዊ ነዉ። ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 17፤እንደተመለከተዉ የባንክ አመራሮችን ማገድ ወይም በአንቀጽ 31 እንደተመለከተዉ ጥፋተኛዉ ባንክ አንዳንድ

የእርምት እርምጃዎችን እንዲወስድ ወይም አንዳንድ የባንክ ስራዎችን እንዳይሰራ ማገድ ወይም በቁጥር 33 በተመለከተዉ መሰረት ባንኩ በሞግዚት እንዲተዳደር ማድረግ ናቸዉ፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2035 መሰረት የባንክ አስተዳደር ሕጎችን መጣስ ጥፋት ቢሆንም ይህን ጥፋት እንደምክንያት በማንሳት ባንኩን ተጠያቂ እንዲሆን ማድረግ የሚችሉት በተጎዱበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከባንኩ ጋር የዉል ግንኙነት የሌላቸዉ ሰዎች ብቻ ናቸዉ፡፡ በዚሁ በፍትሐ ብሔር ሕግ በቁጥር 2037 ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ ዉልን አለመፈጸም ከዉል ዉጭ ሃላፊነት ስለማያስከትል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለዉ አለመግባባት የሚፈታዉ በዉል ሕግ መርሕ መሰረት ብቻ ነዉ፡፡በመሆኑም ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት የባንክ ስራ አዋጅን መሰረት በማድረግ የአባይ ባንክ አ.ማ. ሃላፊነት ለመወሰን መሞከሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ ይህ ስህተት ነዉ ሰበር ሰሚዉን ፍርድ ቤት ሌሎቹን ከታች የምንመለከታቸዉን ተከታታይ ስህተቶች እንዲሰራ ያደረገዉ፡፡

6.2. በአቶ ማርቆስ ጋቴሮና በአባይ ባንክ አ.ማ.ያለዉ ግንኙነት የሚመራዉ በገንዘብ ማዘዋወር ዉል ሕግ እንጂ በገንዘብ ማስቀመጥ ዉል አለመሆኑን በሚመለከት

ክርክሩን ለመወሰን ወሳኝ ድርሻ ያልነበራቸዉ ቢሆንም ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት ሌሎች ሁለት መሰረታዊ የሕግ ስሕተቶችንም ሰርቷል፡፡ እነዚህም የሃዋላ ዉል ገንዘብ በአደራ የማስቀመጥ ዉል ነዉ ማለቱ ነዉ፡፡የሃዋላ አገልግሎት ዉል የሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቱ እንዳለዉ ገንዘብ በአደራ የማስቀመጥ ዉል ሳይሆን የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱ የሃዋላ ገንዘብ ማስተላለፍ ዉል ገንዘብ በአደራ የማስቀመጥ ዉል ነዉ ብሎ ስለወሰደ በንግድ ሕግ ከቁጥር 896 እስከ 902 ያሉትን ድንጋጌዎች ለዉሳኔዉ እንደመንደርደሪያ ተጠቅሟል፡፡ በንግድ ሕግ ቁጥር 896 የተመለከተዉ የባንክ ስራ ዉል የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል ሳይሆን የገንዘብ ማስቀመጥ ዉል ነዉ፡፡ይህም በተለምዶ የቁጠባ ሒሳብ (በጊዜ ገደብ ወይም ያለጊዜ ገደብ) ወይም በቼክ የሚንቀሳቀስ የሚችል የገንዘብ ማስቀመጥ ሊሆን እንደሚችል ከቁጥር 896 እስከ 902 ድረስ ያሉትን ይዘት በተለይ ደግሞ የቁጥር 897 እና 898 በመመልከት መረዳት ይቻላል፡፡ ገንዘብ የማስቀመጥና ገንዘብ ማስተላለፍ ሁለት የተለያዩ የባንክ ስራ አይነቶች መሆናቸዉን የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 2(2ሀ) እና አንቀጽ 2(2መ) በግልጽ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት በንግዴ ህጉ ከቁጥር 896 እስከ 902 ያሉትን ድንጋጌዎች መጥቀሱ በስህተት ነዉ፡፡ የአቶ ማርቆስ ጋትሮ እህት በአሰሪዋ በኩል ከአባይ ባንክ ጋር የገባችዉ የባንክ ስራ ዉል የገንዘብ ማስቀመጥ ዉል ሳይሆን የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል(የሃዋላ አገልግሎት ዉል) ነዉ፡፡ የብሔራዊ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 718/2003 አንቀጽ 2(13) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ

ገንዘብ ማስተላለፍ ማለት በሀዋላ የሚደረግ ማናቸውም የገንዘብ ማስተላለፍንም ይጨምራል፡፡ ፍርድ ቤቱ ሃዋላ የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል መሆኑን ተረድቶ ቢሆን ኖሮ ክርክሩን ለመወሰን ይጠቀም የነበረዉ ሕግ የብሄራዊ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 718/2003 ይሆን እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሃገር ዉስጥ ሃዋላ ከልክሏል፡፡ስለዚህም በተግባር አሁን እየተሰራበት ያለዉ የገንዘብ ማስተላለፍ አይነት በንግድ ሕግ ቁጥር 903 ላይ የተመለከተዉ ብቻ ነዉ፡፡

ምናልባት እንኳ የአቶ ማርቆስ ጋትሮ እህት ገንዘቡ እንዲላክላት ያዘዘችዉ በሊባኖስ ሀገር አባይ ባንክ ዉስጥ ከከፈተችዉ ሒሳብ ቢሆን እና ገቢ እንዲደረግ የታዘዘዉም አቶ ማቲዎስ በአባይ ባንክ በከፈቱት ሂሳባቸዉ ቢሆን ኖሮ ለዚህ ትክክለኛዉ የባንክ ስራ ዉል ሕግ የባንክ ሂሳብ ስለማዘዋወር የሚለዉ ከቁጥር 903 እስከ ቁጥር 912 ያለዉ ድንጋጌ ነዉ፡፡በርግጥ የክሱ ዋና ጭብጥና ዉዝግብም የተከሰተዉ ገንዘቡ ወደ አቶ ማርቆስ ጋቴሮ ሂሳብ እንዲገባ ሳይሆን በእጃቸዉ እንዲሰጣቸዉ የታዘዘ በመሆኑ ነዉ፡፡ ወደ ሂሳባቸዉ እንዲገባ ቢሆን ኖሮማ ሃሰተኛ መታወቂያ የያዘ ሰዉ ገንዘቡን ባልወሰደና ክርክሩም ባልተነሳ ነበር፡፡በርግጥ የኢትዮጵያ ባንኮች ዉጭ ሀገር ቅርንጫፍ መክፈት ስለማይፈቀድላቸዉ አባይ ባንክ ሊባኖስ ቅርንጫፍ አይኖረዉም፡፡ ለአቶ ማርቆስ የተላከዉ ገንዘብ ሊባኖስ ካለ ሌላ ባንክ ዉስጥ ካለ ሂሳብ ተቀንሶ ነዉ ሊያስብል የሚያስችል ማስረጃ በክርክሩ ላይ የማይታይ ከመሆኑም ባሻገር አባይ ባንክ አ.ማ. ባለ የአቶ ማርቆስ ቴሮ ሂሳብ ገቢ እንዳልተደረገ በክርክሩ ላይ በግልጽ የሚታይ ነዉ፡፡ከዚህም በላይ ንግድ ሕግ ቁጥር 903(1) በባንክ ያለዉን ሂሳብ ማዘዋወርን በጠባቡ በመተርጎም ገንዘብ የሚያዘዋወረዉ በአንድ ባንክ ዉስጥ ባሉ ሁለት ሂሳቦች መካከል እንደሆነ ስለሚደነግግ በአቶ ማርቆስ ጋቴሮና በአባይ ባንክ አ.ማ.መካከል ያለዉ ክርክር የባንክ ሂሳብ ስለማዘዋወር የሚለዉ ከቁጥር 903 እስከ ቁጥር 912 ባለዉ ድንጋጌ አይመራም፡፡ በአጭሩ በአቶ ማርቆስ ጋቴሮና በአባይ ባንክ አ.ማ. ያለዉ ግንኙነት የሚመራዉ በገንዘብ ማዘዋወር ዉል ሕግ መሰረት ነዉ፡፡

6.3 ባለእዳ እዳዉን እንደከፈለ የሚቆጠረዉ ክፍያዉን ለመቀበል ሕጋዊ መብት ላለዉ ሰዉ ሲከፈል ነዉ፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በአቶ ማርቆስ ጋቴሮና በአባይ ባንክ አ.ማ. መካከል ያለዉ ክርክር የሚፈታዉ በገንዘብ ማዘዋወር ዉል ሕግ መሰረት መሆኑን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡አሁን ደግሞ ለመሆኑ ጉዳዩ በገንዘብ ማዘዋወር ዉል ሕግ መሰረት ቢመራ ኖሮ ዉጤቱ የተለየ ይሆን ነበርን የሚለዉን እንመረምራለን፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ዉስጥ ስለ ገንዘብ ማዘዋወር ዉል የሚደነግግ ሕግ የለም፡፡ የባንክ ስራ ዉል ሕግ የሚመለከተዉ የንግድ ሕጉ አንቀጽ ሶስት ስር የተደነገጉት የባንክ ስራ ዉሎች ሰባት ብቻ ናቸዉ፡፡ እነዚህም ለባንክ የሚሰጡ አደራዎች ዉል (ገንዘብን በአደራ ስለማስቀመጥ፡የባንክ ሂሳብን ስለማዘዋወር፡ሰነዶችን በአደራ ስለማስቀመጥ) የካዝና ኪራይ ዉል፤ የተመላላሽ ሂሳብ ዉል፤ የቅናሽ ዉል እና ብድር ስለሚያስጡ ግንኙነቶች ዉል(የብድር መከፈት፡ ሰነድ አስይዞ ገንዘብ ስለመበደር፡በሰነድ ስለሚሰጡ ብድሮች)፡፡ በመሆኑም የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል በአጠቃላይ በሓዋላ ገንዘብ የማስተላለፍ ዉል በተለይ በንግድ ሕግ ዉስጥ ሳይደነገጉ ቀርተዋል ማለት ነዉ፡፡ ምናልባትም ይህ ሊሆን የቻለዉ የንግድ ህጉ በወጣበት ጊዜ ገንዘብ የማስተላለፍ ስራ ብዙም ያልተለመደ የባንክ ስራ ስለነበረ ሊሆን ይችላል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በተዘዋዋሪም ቢሆን በሃዋላ የገንዘብ ማስተላለፍ ዉልን የሚመለከተዉ ሕግ የብሔራዊ የክፍያ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 ነዉ፡፡በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(16(ሀ) ስር እንደተመለከተዉ የብሄራዊ የክፍያ ስርዓት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ገንዘብ ወይም የክፍያ ትዕዛዞችን መላክ፣ መቀበል፣ ክፍያ ማካሔድ ወይም ማስተላለፍን በዋናነት ይመለከታል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(13) ገንዘብ ማስተላለፍ ማለት በሓዋላ የሚደረግ የገንዘብ ዝዉዉርንም ይጨምራል፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 19 ላይ እንደተመለከተዉ ገንዘብ አስተላላፊ "ከ...ገንዘብ ማስተላለፍ ጋር... በተያያዘ ለሁሉም ተገልጋዮች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆን ግልጽና ወጥ የሆነ ናሙና የውል ግዴታዎች ተገልጋዮቹ መርምረው መስማማት እንዲችሉ አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት፡፡" ይህ የሚያመለክተዉ የገንዘብ አስተላላፊዉ ባንክና የገንዘብ አስተላላፊዉ ግንኙነት የሚመራዉ በገንዘብ ማስተላለፍ ዉል መሰረት ነዉ ማለት ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት የአቶ ማርቆስ ጋቴሮና የአባይ ባንክ አ.ማ. ክርክር መዳኘት የሚገባዉ በገንዘብ ማስተላለፍ ዉላቸዉ መሰረት ነዉ፡፡ ተከራካሪዎቹም ሆኑ ሰበር ሰሚዉ ፍርድ ቤት(እንዲሁም የታችኞቹ ፍርድ ቤቶች) ይህን ሳያነሱ መቅረታቸዉና የባንክ ስራ አዋጅን በመጥቀስ ባንኩ ጥፋተኛ ነዉ ወይም አይደለም በማለት መከራከራቸዉ ስህተት ነዉ፡፡የባንክ ስራ አዋጅ ባንኮች ለደንበኞቻቸዉ ማድረግ ስለሚኖርባቸዉ ጥንቃቄ የሚናገረዉ ነገር የለም፤ሰበር ሰሚዉም ፍርድ ቤትም ይህን ያመለክታል ያለዉን አንቀጽ አልጠቀሰም፡፡

ለመሆኑ "በአቶ ኤልያስ ኢሌሀበር እና በአባይ ባንክ አ.ማ. መካከል ያለዉ የሃዋላ ዉል ስለተፈጠረዉ ችግር ምን መፍትሔ ይሰጣል?" የሚለዉ በቀዳሚነት ሊመረመር የሚገባዉ ነዉ፡፡ ይህ ዉል ለጉዳዩ እልባት የማይሰጥ ከሆነ የመጨረሻ አማራጭ የሚሆነዉ የፍትሐ

ብሔር ሕግ ስለዉል በጠቅላላዉ የሚለዉን ለመጠቀም እንገደዳለን፡፡በክርክሩ ሒደት ስለዉሉ ይዘት የቀረበ ነገር ስለሌለ ጉዳዩን ከፍትሐ ብሄር ሕግ መሰረት ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት አቶ ማርቆስ ጋቴሮ ባንኩን የመክሰስ መብት እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ስንመረምር መልስ ልናገኝ የምንችለዉ ከፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1957 እና 1961 ነዉ፡፡ ይህ ማለት እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች አቶ ማርቆስን ባለገንዘብ ሲያደርጉት አባይ ባንክ አ.ማ. ደግሞ ባለእዳ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡ባለእዳ እዳዉን መክፈል ያለበት ለማን እንደሆነ ለማወቅ ደግሞ የፍትሐ ብሔር ቁጥር 1741-1744 ያሉትን ድንጋጌዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡በአቶ ማርቆስ ጋቴሮ እና በአባይ ባንክ አማ መካከል ያለዉን ግንኙነት በቀጥታ የሚመለከተዉ የመቀበል መብት ለሌለዉ ሰዉ ስለመክፈል የሚለዉ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1743 ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የመቀበል መብት ለሌለዉ ሰዉ የተከፈለ ክፍያ ባለእዳዉን ከእዳዉ ነጻ የሚያወጣዉ ባለገንዘቡ ክፍያዉን ካጸደቀዉ ወይም ከክፍያዉ ተጠቃሚ ከሆነ ወይም **በማያጠራጥር አኳኋን ባለገንዘቡን መስሎ ለተገኘ ሰዉ በቅን ልቦና ከፍሎ የተገኘ** እንደሆነ ነዉ፡፡(ትኩረት በጸሃፊዉ)

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ባለእዳዉ ከእዳዉ ነጻ እንዲሆን ከፈለገ እዳዉን ሲከፍል ሁለት መስፈርቶችን በጣምራ እንዳሟላ ማስረዳት አለበት፡፡አንደኛዉ መስፈርት ክፍያዉን ሲከፍል እንዳይከፍል የሚያደርግ ምንም የሚያጠራጥር ነገር እንዳልነበር ማስረዳት ይኖርበታል፡፡ እዚህ ጋር የሚመጣዉ ጥያቄ "ባለእዳዉ ይህን እንዴት ሊያስረዳ ይችላል?" የሚለዉ ነዉ፡፡ በአቶ ማርቆስ ጋቴሮና በአባይ ባንክ መካከል ባለዉ ክርክር ባንኩ ይህን ያስረዳዉ ገንዘቡን የወሰደዉ ሰዉ ባለገንዘብ መሆኑን የሚያሳይ መታወቂያ እና ለተላከለት ሰዉ ብቻ በላኪዉ የሚሰጥ የሚስጢር ቁጥር አቅርቧል፡ በማለት ነዉ፡፡ነገር ግን ይህ ማስረጃ ገለልተኝነት(neutrality)ና ወጥነት(objectivity) ይጎድለዋል፡፡ገለልተኝነት የሚጎድለዉ መታወቂያዉን በደንብ አይቼዋለሁ እያለ ያለዉ እራሱ ባንኩ እንጂ ይህን ባግባቡ ስለማድረጉ ምንም ያቀረበዉ ማስረጃ የለም ፤ በአግባቡ አላየምም ሊሆን ይችላል፡፡ አይቶታል ቢባል እንኳ መታወቂያዉ የተጭበረበረ ሆኖ የተገኘ በመሆኑ ምናልባት መታወቂያዉን ክፍያዉን ከከፈለዉ ሰራተኛ ዉጭ ያለ ሌላ ሰራተኛ አይቶት ቢሆን ኖሮ የተጭበረበረ መሆኑን ሊረዳ ይችል ይሆናል፡ ምክንያቱም ሁላችንም እኩል ጉድለትን የማስተዋል ብቃትና ተሰጥኦ የለንምና፡፡ በመሆኑም አጠራጣሪ ነዉ ወይስ አያጠራጥርም ነበር የሚለዉ የግላዊነትማንነት(subjectivity) መስፈርት ላይ እንዲንጠለጠል ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ባለእዳዉ ገንዘቡን የከፈለዉ ምንም ጥርጣሬ ሳይኖረዉ ነበር የሚለዉን በማያጠራጥር ሁኔታ ለማሰረዳት አስቸጋሪ ነዉ፡፡ ሌላዉ ለባለእዳዉ ለማስረዳት

የሚያስቸግረዉ ነገር ክፍያዉን የፈጸመዉ በቅን ልቦና መሆኑን እንዴት እንደሚያስረዳ ነዉ።በቃለ መሃላ ነዉ የሚያስረዳዉ ወይስ ምስክሮችን በማቅረብ፡ምስክሮችስ ቀርበዉ ምንድነዉ የሚመሰክሩት?

ከዚህ በመነሳት በማያጠራጥር ሁኔታ ባለገንዘብ መስሎ ለተገኘ ሰዉ የሚለዉን ሀረግ ገለልተኛና ወጥነት ባለዉ ማስረጃ ማስረዳት ከተቻለ ብቻ ባለእዳዉ ከእዳዉ ነጻ ይወጣል ብሎ መተርጎም የበለጠ ወደ እዉነታዉ የተጠጋ ይሆናል።የማስረዳት ሸክሙንም መጀመሪያ በባለእዳዉ ላይ ቀጥሎ ደግሞ በባለገንዘቡ ላይ በማድረግ ምክንያታዊ የሆነ መደምደሚያ ላይ መድረስ ይቻላል፤፤ በዚህም መሰረት ባለእዳ ማቅረብ ያለበት ማስረጃ ገንዘቡን የተቀበለዉ ሰዉ ገንዘቡን በተቀበለበት ወቅት ፍጹም ባለገንዘብ መስሎ እንዲታይ የሚያደርገዉ ህጋዊ ሰነድ ይዞ የቀረበ መሆኑን የሚያሳይ መሆን አለበት። ለምሳሌ ገንዘብ እንዲቀበል የተወከለበት ትክክለኛ የዉክልና ስልጣን ነገር ግን ለባለእዳዉ ባያሳዉቅም ባለገንዘቡ ክፍያዉን ተወካይ ከመቀበሉ በፊት ተሸሮ የነበረ ወይም ጠፍቶ የተገኘ ወይም የተሰረቀ ለታዘዘለት/ላምጪዉ የሚከፈል የንግድ ወረቀት፤የወራሽነት ማስረጃ ከመሻሩ በፊት ወይም መሻሩንም ባለእዳዉ የማያዉቅ ከሆነ።

ባለእዳ በእነዚህ ህጋዊ ሰነዶች መሰረት እንደከፈለ ካስረዳ ክፍያዉ የተፈጸመዉ ከቅን ልቦና በተቃራኒ ነዉ የሚለዉን ደግሞ ባለገንዘቡ የማስረዳት ሃላፊነት ይወስዳል ማለት ነዉ። ባለገንዘቡም ይህንን በምስክርም ሆነ በማንኛዉም አካባቢያዊ ማስረጃ ማስረዳት ይችላል። ለምሳሌ ዉክልናዉ እንደተሻረ በስልክ ወይም በኢሜል እንደነገረዉ፡ ቼኮቹ እንደተሰረቁበት/እንደጠፉበት እንደስታወቀዉ፤የወራሽነት ማስረጃዉን በስህተት የተገኘ መሆኑን እንደነገረዉ የመሳሰሉትን በማስረዳት ባለእዳዉ እኔ አልጠየቅም የሚል እምነት ይዞ(ሰነዶቹ ህጋዊ ስለሆኑ ብቻ) በግዴለሽነት ወይም ባለገንዘቡን ለመጉዳት በማሰብ ገንዘቡን ሰነዱን ለያዘዉ ሰዉ መክፈሉን በማሳየት ባለእዳዉ ክፍያዉን ሲፈጽም ቅን ልቦና እንዳልነበረዉ ማሳየት ይችላል።

የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1744 በዚሁ አተረጓጎ መሰረት የተደነገገ ድንጋጌ እንደሆነም መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሁለት እና ከዚያን በላይ የሆኑ ሰዎች በየፊናቸዉ ገንዘቡ ይገባናል እያሉ የሚጠይቁ ከሆነ ባለእዳዉ ገንዘቡን መክፈል ያለበት ለፍርድ ቤት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ይህ ሁኔታ የተጨበረበረ ሰነድ ያመጣን ሰዉ የሚመለከት ሳይሆን ህጋዊ ሰነድ የያዘን ገንዘብ ጠያቂ ላይ የቀረበን ተቃዉሞ የሚመለከት ስለመሆኑ ግልጽ ነዉ። ህጋዊ ሰነድ የያዘዉ አንደኛዉ ሆኖ ሌሎቹ ደግሞ ይህን ሕጋዊ ሰነድ መቃወም

የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ሁሉም ሕጋዊ ሰነድ ያላቸዉ ግን አንዳቸዉ የሌላዉን ሰነድ መብት ያሰጣል ብለዉ የማይቀበሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

6፡4 ባለእዳ እዳዉን መወጣቱን ማስረዳት ይኖርበታል (ለባለገንዘቡ መክፈሉን የማስረዳት ሸክም አለበት)

ይህን ጉዳይ ከማስረጃ ሕግ አኳያም መመርመር ተገቢ ነዉ፡፡በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2001(1) ላይ እንደተመለከተዉ በባለገንዘብ ግዴታ ዉል መኖሩን ማስረዳት ብቻ ነዉ፡፡ግዴታዉን ለባለገንዘቡ መፈጸሙን የማስረዳት ግዴታ የባለእዳዉ እንደሚሆን በዚሁ ሕግ ቁጥር 2001(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ በአቶ ማርቆስ ጋቱሮና በአባይ ባንክ አ.ማ.መካከል ባለዉ ክርክር አቶ ማርቆስ ባለገንዘብ ሲሆን ባንኩ ደግሞ ባለእዳ ነዉ፡፡አቶ ማርቆስ ከባንኩ ላይ የሚጠይቀዉ መብት እንዳለዉ አስረድቷል፡፡ አቶ ማርቆስ ገንዘቡን መቀበሉን ማስረዳት የባንኩ ግዴታ ነዉ፡፡ ባንኩ ደግሞ አቶ ማርቆስ አለመቀበሉን አምኗል፤ይህ ማለት ለባለገንዘቡ መክፈሉን አላስረዳም፡፡ ታዲያ እንዴት ነዉ ከግዴታዉ ነጻ የሚሆነዉ? አንድ ባለእዳ ከእዳዉ ነጻ የሚሆነዉ እዳዉን ለባለገንዘቡ መክፈሉን በማስረዳት እንጂ ክፍያዉን ባይፈጽምም እንኳ ያልከፈለዉ በእርሱ ጥፋት አለመሆኑን በማስረዳት አይደለም፡፡ በመሆኑም ባንኩ ግዴታዉን ለባለገንዘቡ መወጣቱን ስላላረጋገጠ ከተጠያቂነት አያመልጥም፡፡

7. ማጠቃለያ

ይህ ክርክር ሲጠቃለል አቶ ጋትሮ ባለገንዘብ መሆኑ እየታወቀና ይህም ገንዘቡ በባለእዳዉ(በባንኩ) እጅ እያለ ስለተሰረቀ ኪሳራዉ ያንተ ነዉ መባሉ ትክክል አይደለም፡፡ በባንኩ ዘንድ ያለዉን ገንዘቡን በማሰረቅ አቶ ጋተሮ ተባብሯል ቢባል እንኳ(ይህ አልተረጋገጠም እንጂ) ክርክሩ መሆን የነበረበት ከክፍያዉ ተጠቅሟል ወይም ለደረሰዉ ጉዳት አስተዋጽኦ አድርጓል የሚል እንጂ ባንኩ ጥፋት የለበትም የሚል አይሆንም፤ይህ ማለት የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ መሰረት ማድረግ የነበረበት የአቶ ጋትሮን ጥፋት እንጂ የባንኩን ታታሪነት መሆን አይገባም ነበር፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን የተሳሳተ ዉሳኔ ሊያስተላልፍ የቻለዉ ክርክሩን ተገቢ ባልሆነ ሕግ በመምራቱ ነዉ፡ ክርክሩ የዉል አለመፈጸም(የገንዘብ ማስተላለፍ ዉል) ሆኖ እያለ የባንክ ስራዎች አስተዳደር ሕግን(ባንኪንግ ቢዚነስ ሬጉሌሽን) መሰረት አድርጎ ክርክሩን በመወሰኑ ነዉ፡፡